Washington State Governor's Office of the Education Ombuds

P.O. Box 40004
Olympia, WA 98504
የነፃ ስልክ መስመር: 1-866-297-2597

ድረገፅ: www.oeo.wa.gov
ኢሜይል: oeoinfo@gov.wa.gov
ፋክስ 1-844-886-5196

# Washington State Governor's Office of the Education Ombuds (ከዋሽንግተን ግዛት ገዥ የትምህርት እምባ ጠባቂ ጽ/ቤት) ጋር መሥራት

Washington State Governor's Office of the Education Ombuds (OEO) (የዋሽንግተን ግዛት ገዥ የትምህርት እምባ ጠባቂ ጽ/ቤት (OEO)) ስላነጋገሩ እናመሰግናለን። እኛ ከእርስዎ ወይም ከእናንተ ጋር ለመስራት ስንስማማ ደስታ ይሰማናል። ይህ ገጽ ስለጽ/ቤታችን የተወሰኑ ጠቃሚ መረጃዎችን ይሰጣችኋል።

የ OEO ሠራተኞች የተማሪዎች የመማር ሂደት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮች ለመፍታት በግዛቱ ውስጥ ባሉ ቤተሰቦችና ትምህርት ቤቶች ጋር የሚሰሩ 5 የትምህርት እምባ ጠበቂዎች ናቸው። እኛ የውይይት እና የመተባበር የችግር አፈታት ዜዴን የሚናመቻች ቢሆንም እኛ አስፈጻሚ ወይም አስገዳጂ ድርጅት ወይም ተቋም አይደለንም,።

**የትምህርት እምባ ጠባቂ:**

- ከተማሪዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው የእናንተን ጥያቄዎችና የሚያሳስቡ ጉዳዮች ለመረዳት ያዳምጣል፣
- ስለ የህዝብ ትምህርት ቤት ሂደቶች እና የተማሪዎችና የወላጆች መብቶችና ግዴታዎች የሚመለከቱ መረጃዎች ይሰጣል፣ ወደተገቢ  መገልገያዎች ያስተላልፋል፣
- አስጊ ጉዳዮችን ለመፍታት ያስችላሉ ተብለው የታሰቡትን አማራጮች ለመለየት፡ ለመረዳት  እና ለመገምገም እርስዎን ለማገዝ ጥያቄዎች ይጠይቃል፣
- እንደ ገለልተኛ አወያይ ቦርድ ያገለግላል፣
- ግጭትን በመፍታት እና ውጤታማ ግንኙነት በመገንባት ረገድ ድጋፍ እና ሥልጠና ይሰጣል፣
- ያሉትን ችግሮች ግልጽ ለማድረግ እና በቤተሰቦችና በትምህርት ቤቶች መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖር ለማመቻቸት ከቤተሰቦች፡ ከመምህራንና ከሌሎች አካላት ጋር ይመካከራል፣ እና
- የቤተሰብ ተሳትፎን በትምህርት ቤቶች ለማሳደግ ጥሩ ተሞክሮዎችን ያጋራል።

OEO ገለልተኛ የግዛት ድርጅት ነው።

የምንሰጣቸው አግልግሎቶች:

- ✓ ነፃ
- ✓ ሚስጥራዊ
- ✓ ከአድልዎ ነፃ
- ✓ የትብብር ሲሆን
- ✓ ልጃቸውን በዋሽንግተን ግዛት ከመዋዕለ ሕፃናት - 12 በመንግስት ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ ቤተሰቦች፣ መምህራን እና ሌሎች አካላት እንሰጣለን።

OEO ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች ሚስጥራዊ ሲሆኑ OEO ከወላጅ ወይም ከህጋዊ ሞግዚት ወይም ከአዋቂ ተማሪ  በቅድሚያ በጽሁፍ ፈቃድ ወይም ስምምነት ሳያገኝ ስለ ደዋዩ ወይም ተማሪ ምንም አይነት መረጃ ይፋ አያወጣም። OEO **የቅድሚያ የጽሁፍ ስምምነት** ከተቀበለ እምባ ጠባቂው በቀጥታ ከትምህርት ቤት ወይም የዲስትሪክት ሠራተኛ ጋር በመነጋገር ችግሮችን ግልጽ ለማድረግ እና ለመፍታት እገዛ ለማድረግ ሊሞክር ይችላል። ያሉት ሀብቶች ውስን በመሆናቸው ምክንያት እምባ ጠባቂው ስብሰባዎችን በአካልም ሆነ በስልክ ለመከታተል አልፎ አልፎ የሚችል ቢሆንም የተወሰኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ለአንድ ስብሰባ ተገኝቶ በመከታተል በቤተሰቦችና በትምህርት ቤቶች መካከል የጋራ ግንዛቤ እና ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖር መንገድ ለማመቻቸት ያግዛል።

**የትምህርት እምባ ጠበቂ የሚከተሉትን አያከናውንም:**

- የህግ ማማከር ወይም የውክልና አገልግሎት አይሰጥም፣
- ግለሰብ ተማሪም ሆነ ወላጅን ጨምሮ ለማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ጠበቃ ሆኖ አያገለግልም፣
- ህጎችም ሆነ የደንቦች ማስፈጸም ስራ አይሰራም፣
- መደበኛ ምርመራዎች አያከናወንም፣ ወይም የምርመራ ውጤቶች አይሰጥም፣ ወይም
- ትምህርት ቤቶችም ሆኑ ዲስትሪክቶች ማንኛውንም የተወሰነ እርምጃ እንዲወስዱ ወይም እንዳይወስዱ ለማስገደድ ስልጣን የለውም።

OEO የተወሰነ መፍትሔ ለማስገኘት ዋስትና መስጠት አይችልም፣ ነገር ግን እኛ ሁልጊዜ የእናንተን ችግሮች ለመረዳት፡ አግባብነት ያላቸው እና ትክክለኛ መረጃዎችን ማጋራት እንዲሁም ተማሪዎቹን ለማገዝ የትብብር የችግር አፈታት አማራጮችን ለመለየት እንሠራለን። እንደ አነስተኛ የግዛት ድርጅት እኛ ባለን ሀብት መጠን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለመስራት ጥረት እናደርጋለን። እምባ ጠባዊ በግለሰብ ጉዳዮች ላይ ገደብ የለሽ ወይም የረጅም ጊዜ ድጋፍ መስጠት አይችልም።

የሰራተኞች ቁጥር ውስን በመሆኑ፣ ከአንድ ተማሪ/ቤተሰብ ጋር መስራት የማንችለው በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ ይህም በስልታዊ እቅዳችን ጊዜ ውስጥ ለሚያርፉ ቢበዛ ለ120 ቀናት ውስጥ ነው።

Governor's Office of the Education Ombuds

**P.O. Box 40004**
**Olympia, WA 98504**
ነጻ የስልክ መስመር:  1-866-297-2597

**www.oeo.wa.gov**
ኢ-ሜይል: oeoinfo@gov.wa.gov
የፋክስ ቁጥር: 1-844-886-5196

# ትምህርት ቤቶችን እና ዲስትሪክትን ለማግኘት ፍቃድ መጠያቂያ

ኦ ኢ ኦ የርስዎን እና የማንኛውንም ተማሪ የግል ማህደር ለሌሎች አሳልፎ አይሰጥም። ከእኛ ጋር የሚያደርጉት ውይይት በሚስጥር ነው የሚይዘው። በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር እንዲሁም እርስዎን የሚመለከቱ ማንኛውንም አይነት መረጃ እርስዎ በጽሁፍ ፍቃድ ካልሰጡን በስተቀር ለሌላ ወገን አሳልፈን አንሰጥም።

ከትምህርት ነክ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ እምባ ጠባቂዎች (ኤጁኬሽን ኦምባድስ) ጋር ተነጋግረው ካበቁ በሁዋላ የእምባ ጠባቂው አባላት ልጆዎት የሚማርበትን/የምትማርበትን ትምህርት ቤት እና ዲስትሪክት እንዲያገኙ የሚፈቅዱ ከሆነ የእምባ ጠባቂዎቹ ቡድን አስቀድሞ **<u>ፍቃድ እንደሰጡ የሚገልጽ የስምምነት ውል በጽሁፍ</u>** ማግኘት ያስፈልጋቸዋል።

- **የእምባ ጠባቂው ሰራተኞች (ኦምባድስ) ልጆዎት የሚማርበትን/የምትማርበትን ትምህርት ቤት እና/ወይም ዲስትሪክት እንዲያገኙ የሚፈቅዱ ከሆነ <u>ይህንን ፎርም ካነበቡ በሁዋላ ፈርማው ወደ እኛ ይመልሱት።</u>**
- **ይህንን ፎርም ከፈረሙ በሁዋላ ቅጂውን ወደ ኦ ኢ ኦ በፖስታ ከላይ ወደ ተጠቀሰው አድራሻ ወይም በኢ-ሜይል ወደ OEOinfo@gov.wa.gov ወይም በፋክስ ቁጥር 1-844-886-5196 ይላኩት።**

---

**የዛሬው ቀን** ______________________

**እኔ ከዚህ በታች የተቀሰው/የተጠቀሰችው ተማሪ [] ወላጅ ወይም [] ህጋዊ አሳዳጊ ነኝ።**

**እኔ እድሜዬ 18 ወይም ከዛ በላይ የሆንኩ [] ተማሪ ነኝ።**

የትምህርት ነክ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ እምባ ጠባቂዎች ቢሮ (ኦፊስ ኦፍ ኤጁኬሽን ኦምባድስ) ነጻ እና ገለልተኛ ሆኖ የተማሪዬን ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች መፍትሄ ለማግኘት ይጥራል እንጂ ህጋዊ የውክልና ወይም የምክር አገልግሎት እንደማይሰጠኝ እረዳለው።
የትምህርት ነክ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ እምባ ጠባቂዎች ቢሮ ሰራተኞች (ኦፊስ ኦፍ ኤጁኬሽን ኦምባድስ ኤንድ ስኩል/ዲስትሪክት ስታፍ) እና የትምህርት ቤት/ዲስትሪክት አባላት ያጋጥሙኝን ቅሬታዎች/ችግሮች መፍትሄ ለማግኘት እንዲረዳ የእኔን/የተማሪዬን ስም እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በመመልከት ይህን ጉዳይ እንዲመለከቱ የፈቀድኩ መሆኔን እገልጻለው።

| | |
|---|---|
| ______________________________ | ______________________________ |
| **የትምህርት ቤቱ ስም** | **የትምህርት ቤቱ ስም** |
| ______________________________ | ______________________________ |
| **የተማሪው/የተማሪዋ ስም** | **የተማሪው/የተማሪዋ የትውልድ ቀን** |
| ______________________________ | |
| **የወላጅ/የህጋዊ አሳዳጊ ስም** | |
| ______________________________ | ______________________________ |
| **የወላጅ/የህጋዊ አሳዳጊ ፊርማ** *ወይም* | **የተማሪው/የተማሪዋ ፊርማ(እድሜው/እድሜዋ 18 ወይ ከዛ በላዩ የሆነ)** |